# ዜማ ይወጽእ እምያሬድ ዘኢትዮጵያ

# ወቃለ እግዚአብሔር እምኢየሩሳሌም

ይህንን ያሬዳዊ ዜማ አሁን ዘመኑ ባፈራው ጥበብ ወደ ድምፀ መዛግብት (digital) ለመቀየር ያነሳሱን ምክንያቶች .

፩ኛ - በሀገር ቤት ያሉ የቆሎ ተማሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እጅግ እየቀነሰ በመሄዱና ይህም አባቶቻችን ሊቃውንት በብዙ ድካም ያቆዩልንን በገንዘብ ሊገዛና ሊተመን የማይቻል ታላቅ ቅርስ ድንገት እንዳይጠፋ . ድካማቸው ሁሉ ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርናብሎም ለዘመነ ዘመናት ቀጣይ ሆኖ እንዲኖር ለማረጋገጥ

፪ኛ - በውጭ ሀገር ተጠያቂ መምህራን ስለሌሉ በውጭ የሚኖሩ ካህናት በቀላሉ

እያጠኑ መለያየት ሳይኖር ቤተ ክርስቲያን በተዋሕዶ ሃይማኖት እንድትገለገል

፫ኛ - በሀገር ቤት ያሉትን የመምህራን ድካም ለመቀነስና ተማሪዎች በከንቱ የሚያባክኑትን ጊዜ ለማሳጠር

፬ኛ - ትምህርቱን ጀምረው ላቋረጡና እንዲሁም ተምረው ለብዙ ዘመናት ተለይተው ለቆዩ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ ተዘጋጅቷል .

ይህንንም ዕቅድ ወደተግባር ለመተርጎም በሃሣብም ሆነ በጥሪት የረዱንን .

፩ኛ - ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስ የምዕራብ ሸዋ ሊቀ ጳጳስን

፪ኛ - በጎደር በዓታ የአቋቋም ምስክር ት/ቤት መምህር መጋቢ አ'ዕላፍ ክቡር ጥላሁንን ፫ኛ - መጋቤ ትፍሥሕት ዘምሮ አበራን - ፬ኛ . ዲያቆን ግርማ ደምሴን እጅግ እናመሰግናቸዋለን

እንዲሁም በቅርብም ሆነ በሩቅ የሚገኙ ወንድሞቻችን በሃሣብ ሰለደገፉንና ስለ አበረታቱን ከልብ እናመሰግናለ .

በተለይም ደግሞ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ይህን ቃለ እግዚአብሔር በብዙ ድካም የቀረፁልንን እግዚአብሔር ዋጋቸውን ይክፈልልን . ፩ኛ መምህር ቀለሙ እንዳለው .የአቋቋም ፤የቅዳሴ ፤የዝማሪ መዋሥእትና የድጓ መምህር . ፪ኛ - መምህር አስተርአየ ካሣየ የአቋቋም መምህር

የቅዱሳን መላእክትና የጻድቃን ሰማዕታት አማላጅነት፤ የቅድስት ድንግል ማርያም ተራዳ'ዒነት፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረትና ቸርነት ፤ የአበው በረከት አይለየን .

አነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው አሜን .

አዘጋጆች ፤ ፩ኛ -ሊቀ ማዕምራን ቃለ አብ አዱኛ

፪ኛ - ሊቀ ትጉሃን አፈወርቅ መንግሥቴ

ኢየሩሳሌም - እሥራኤል